# የኢትዮ - ኤርትራ ስንክሳር

# The Ethio - Eritrean Predicament

Upcoming Book by

Solomon Barnabas

## ምዕራፍ አስራ ሰባት

# ቀይ ባህርና ጂኦ ፖለቲካው፣

## 5. <u>የቀይ ባህር ጂኦ ፖለቲካ፣</u>

የቀይ ባሕር አካባቢ ከፍተኛ የዓለም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚደረግበት፣ በርካታ መርከቦች በስዊዝ ካናልና በባብኤል ማንዴብ ሸርጦች የሚተላለፉበት፣ በርካታ አገራት ትኩረት ሰጥተውት ፀጥታው የተረጋጋ እንዲሆን የሚጓጉለት፣ በርካታ ያካባቢው አገራት በባሕር መተላለፊያው ላይ ጉልህ የሆነ ተጽእኖ ሊያደርጉበት የሚፈልጉ መተላለፊያ፣ አንዳንዶቹ አገራት ደግሞ ይባስ ብሎም ያካባቢው ሁነኛ አዛዦች ለመሆን የሚፈልጉት ዓለም አቀፋዊ መተላለፊያ ነው። አንዳንዶቹ አገራት ደግሞ ባካባቢው ላይ ተጽእኖ ወይም ኃይላቸውን በማሳየት ሌሎች ተቀናቃኝ አገራትን ሊጎዱበት ይፈልጋሉ። በመሆኑም ያካባቢው አገራት በቀይ ባሕር መተላለፊያ ላይ ምንም ሳንካ እንዲፈጠር አይፈልጉም፣ ሰላማዊ ሆኖ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ተግባራትን ለማከናወን ይመኛሉ። ሆኖም በጥባጭ በተለይም አሸባሪዎች በበዙባት ዓለማችን እንደቀይ ባሕር ዓይነቱ መተላለፊያ የጥቃት ወይም የአሸባሪዎች ዒላማ ለመሆን የተመቻቸ ሊሆን ስለሚችል ጥቃቱን ለማስቀረት አገራት ባካባቢው ላይ ትኩረት ማድረጋቸው የግድ ይላል።

### 5.1. <u>የጂቡቲ ወታደራዊ ሰፈሮች እንድምታ፣</u>

አሜሪካ፣ ያውሮጳ ሕብረት፣ ሩስያ፣ ቻይና፣ ጃፓን ወዘተ… በርቀት ከሚገኙ አገራት መካከል በቀይ ባሕር ላይ ከፍተኛ ትኩረት አድርገው ከሚንቀሳቀሱ አገራት ጥቂቶቹ ናቸው። ከቅርብ አገራት ደግሞ እነ ሳውዲ አረብያ፣ ኢራን፣ ግብጽ፣ የዓረብ ኢምሬት፣ ኳታር፣ እስራኤል፣ ቱርክ፣ ወዘተ… ከፍተኛ ትኩረት የሚያደርጉበትና ፍላጎታቸውንና ኃይላቸውን የሚያሳዩበት አካባቢ ሆኗል። እንደ አሜሪካ፣ ቻይናና ያውሮጳ ሕብረት የመሳሰሉት አገራት ከባሕር ውንብድና /ፓይረሲ/ ጋር በተያያዘ በጂቡቲ ላይ ወታደራዊ ካምፕ መስርተው ከከተሙ ቆይቷል። አሜሪካ ብቻ በጦር አይሮፕላኖች፣ በድሮኖች ወዘተ…የሚደገፍና ወደ 4.500 የሚጠጋ የወታደራዊ ኃይል በጂቡቲ ካሰፈረች ከራርማለች። ቻይናም በዚህችው ትንሽ የምስራቅ አፍሪካ አገር ላይ ወታደራዊ ካምፕዋን ሰርታ ከጨረሰች በኃላ ባሁኑ ወቅት ወደ 10.000 ወታደር በዚህች ትንሽ የአፍሪቃ ቀንድ አገር አስፍራለች። ይህ ወታደራዊ ሰፈር ለቻይና ከአገሯውጭ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመ ወታደራዊ ሰፈር መሆኑ ነው። ጃፓንም እንዲሁ ለአነስተኛ ኃይል የሚሆን ካምፕ አላት። ከ4.000 በላይ ወታደር የሚይዘው የፈረንሳይ ካምፕ ቋሚነቱ አገሪቱ ነጻ ከወጣችበት ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ የቀጠለ ነው። (ሻክሲ.ኮም፣ 2017) አሁን ደግሞ

ሳዑዲ አረብያ <<የየመን ሁቲዎችን እዋጋለሁ!>> በሚል ሰበብ በጂቡቲ ወታደራዊ ካምፕ ለመመስረት ውሏን ተፈራርማ ካምፑን ለማደራጀት እያሸበሸበች ትገኛለች። (ዝኒ ከማሁ፣)

ቀይ ባህር፣ የገልፍ ባህረ ሰላጤና ያካባቢው አገራት፣

ይህ በጂቡቲ ላይ የሚታየው የኃያላን አገራትና ያካባቢው አገራት ወታደራዊ ስብስብ ምን አንድምታ ሊኖረው ይችላል? ብለን ከጠየቅን ሁኔታው በቀላሉ ሊታይ የሚችል አይደለም። አሜሪካኖች በዓረብ ባህረሰላጤና በምስራቅ አፍሪቃ አካባቢ ላይ እየተንሰራፋ የመጣውን የአሸባሪዎች እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር ይፈልጋሉ። ስለሆነም በየእለቱና በየሰዓቱ በድሮኖችና በሳተላይቶች ክትትል እያደረጉ ጥቃት የሚሰነዝሩበት ብሎም ልዕልናቸውን የሚያረጋግጡበት አካባቢ ስለሆነ ካካባቢው በቀላሉ የሚለቁ አይሆኑም። እንዲያውም በጣም



በሚገርም ሁኔታ ከሁለተኛዋ የዓለማችን የኢኮኖሚ ቀዳሚ ከሆነችው አገር ከቻይና ጦር ሰፈር በቅርብ ርቀት የራሳቸውን የጦር ሰፈር አደራጅተው ነው በጂቡቲ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙት። ሁለቱ ኃያላን አገራት በሆነ ትንሽ ጉዳይ ቢጋጩ እንኳን ምን ሊከተል እንደሚችል መገመት በሚያስቸግር ሁኔታ በዚህች ትንስ አገር ቅርብ ለቅርብ ተፋጠው <<ጥቅማችንን ለማስከበር ነው የሰፈርነው>> የሚል አቋም ይዘው መኖር መቀጠላቸው ለኢትዮጵያና ለመሳሰሉት ያካባቢው አገራት እንቅልፍ የሚያስተኛ ሆኖ መገኘት አይኖርበትም። ኤርትራም ብትሆን ይህ በጂቡቲ ላይ የሚታው ሁኔታ ለወደፊቱም ቢሆን በኔ ላይ ምንም የሚያመጣብኝ ሳንካ አይኖርም ብላ የምታስብ ከሆነ የዋህነት ነው።

ጂቡቲ የኢትዮጵያ ሁነኛዋና ወሳኝዋ መተላለፊያ ወደብ መሆኗ ይታወቃል። እንግዲህ በዚህ ትንሽ አገር ላይ ከሚታየው የበርካታ አገራት ወታደራዊ ሰፈር አንጻር ሁኔታውን ስንገመግመው ለኢትዮጵያ ከፍተኛ አደጋ መሆኑን መገንዘቡ አያስቸግርም። በርግጥ ነው ጂቡቲ ሉአላዊ አገር እንደመሆኗ ከነዚህ ወታደራዊ ሰፈሮች ጋር በተያያዘ የምታገኘው የገንዘብ እርዳታና ድጋፍ በቀላሉ የሚገመት አይደለም። ከቻይና ብቻም እንኳን 100 ሚልዮን ዓመታዊ ኪራይ ይሰጣታል። ነገር ግን ጂቡቲ ከዚህ በኪራይ መልክ ከምታገኘው ጥቅም በበለጠ ከኢትዮጵያ በወደቡ አገልግሎት ምክንያት የምታገኘው ጥቅም እጅግ በጣም ከፍተኛ እንደሆነም ይታወቃል። ነገር ግን ይህ ዓይነቱ ጥቅም በጂቡቲ ዘንድ ወታደራዊ ሰፈሮችን ከማቋቋም የሚያግዳት ሆኖ አልተገኘም። ስለሆነም ስጋቱና አደጋው አሁንም እነደቀጠለ ይገኛል።

በኢትዮጵያ መንግስት በኩል አሁንም ስጋቱን ብዙ ትኩረት የሰጠው መስሎ አይታይም። ባካባቢው ከማንኛውንም አቅጣጫ ግጭት የመነሳቱ አጋጣሚ ግን አሁንም ከፍተኛ ይመስላል። ታዲያ የኢትዮጵያ መንግስት በወደቡና ባካባቢው ካለው ጥቅም አንጻር ሲታይ <<እኔም ጥቅሜን ለማስጠበቅ በአገሪቱ ውስጥ ወታደራዊ ሰፈር ያስፈልገኛል>> ብሎ እንቅስቃሴ አለመጀመሩ ሁኔታውን ከምን አኳያ እንደገመገመው የሚታወቅ ጉዳይ አይደለም። ነገር ግን ከጥቅም አንጻር ነውና በርካታ አገራት በጂቡቲ ላይ ወታደራዊ ሰፈር በማቋቋም ላይ የሚገኙት ኢትዮጵያም ይህንኑ ድርጊት ከመፈጸም የሚያግዳት አንዳችም ምክንያት አልነበረም። በርግጥ ነው ኢትዮጵያ በቅርብ ርቀት ስለምትገኝ <<የሆነ ችግር ቢደርስ እደርስበታለሁ!>> ብላ ከሆነ ችላ ያለቸው የዚህ ዓይነቱ አካሄድ ንዝህላልነት ካልሆነ በስተቀር ተገቢነት የለውም። ኢትዮጵያ በጂቡቲ ወታደራዊ ሰፈር እንዲኖራት ማድረጉ ራሱ በሌሎች አገራት አካሄድና አመለካከት ላይ ሊኖረው የሚችለው አንድምታ በጥልቀት መታት ነበረበት። ይህ አለመሆኑ ግን ችግር መሆኑን የኢትዮጵያ መንግስት ሊገነዘበው ይገባል።

የሁለቱ አገራት የኢኮኖሚ ትስስር ከፍተኛ መሆኑና በመካከላቸው ችግር ሊፈጠር እንደማይችል መደምደም ቢቻልም በጂቡቲ ውስጥ ችግርና እንቅፋት ሊፈጠር የሚችለው በውጭ ኃይሎች ጣልቃ ገብነትና ተጽእኖ መሆኑን አለማጤን ግን የዋህነት ነው። ያንድ ቀን እንቅፋት በኢትዮጵያ ላይ ሊፈጥረው የሚችለው ጫናና ተጽእኖ ምን ያህል እንደሆነ ከመንግስት በላይ የሚያውቀው ሰው ያለ አይመስለኝም። <<አይሆንም ትተሽ ይሆናል ባልሽ!>> የሚለውን አባባል እንዳያጋጥመን በመንግስት በኩል አስተውሎ መንቀሳቀሱ ተገቢ ይመስለኛል።

## 5.2. ኢትዮጵያ፣ ጂቡቲና ኤርትራ፣

ሌላው እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት ጉዳይ ከኤርትራ ወደቦች አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ያለው ሁኔታ ነው። ጂቡቲ የኤርትራ ወደቦች ሊጠቀሙበት ያልቻሉትን እድል በግላጭና በምትፈልገው መንገድ ከኢትዮጵያ እያገኘችው እንደሆነ ያደባባይ ምስጢር ነው። የኤርትራ መንግስት ከኢትዮጵያ ጋር በፈጠረው ግጭትና አተካሮ ምክንያት ጂቡቲ ሁኔታዎችን ለኢትዮጵያ አመቻችታ መጠቀም ከጀመረች 20 ዓመት ሊሆናት ነው። <<በሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጥበታል!>> እንደሚባለው ዓይነት የኤርትራ መንግስት <<ኢትዮጵያን በጉረሮዋ ይዤ አሰቃያታለሁ! እጠቀምባታለሁ!>> በማለት ያሰላውን መንገድ ወንዝ የማያሻግር ስልት ሆኖ ቀረ። ጂቡቲ ከኤርትራ መገንጠልና የኤርትራ ወደቦችንም ኢትዮጵያ መጠቀምን ካቋረጠችበት ጊዜ ጀምሮ በደጃፍ ላይ ወድቆ የተገኘ ሲሳይ ሆኖላትና የጂቡቲ ወደብን በማስፋፋት፣ በማደራጀትና አሰራሩን በማቀላጠፍ ከፍተኛ ገቢ የምታገኝበትን መንገድ ፈጥራለች። ጂቡቲ ባሁኑ ጊዜ ከኢትዮጵያ የምግብ ምርቶችን፣ የመጠጥ ውሃን፣ የኤሌክትሪክ መብራህትን፣ ፍራፍሬን፣ ጫትን፣ ወዘተ... በየቀኑ በመውሰድ የሕዝቧን ጥቅም እያሟላች ትገኛለች። ጂቡቲ ለዜጎቿ ኢትዮጵያ ሁለተኛ አገራቸው አድርገው እንዲቆጥሯት አደራጅታቸዋለች። ኢትዮጵያም ብትሆን

ጂቡቲ በሯ ብቻ ሳትሆን የደም ስሯም አድርጋ ታስባታለች። የኢኮኖሚ ትስስሩ በጣም ከፍተኛ ነው። ስለሆነም ሁለቱም አገራት እርስ በርሳቸው የተሳሰሩበትና መለያየትም ከማይቻላቸው ደረጃ ላይ የደረሱ ይመስላሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያና ጂቡቲ ከኢኮኖሚ መተሳሰር ወደ ኢኮኖሚ ውሕደት ለመድረስ የሚያስችላቸውን አቅጣጫን ተከትለው እየሄዱ እንዳሉም ካንዳንድ ሁኔታዎች መገንዘብ ይቻላል። ከኢኮኖሚ ትስስሩ በተጨማሪ በመንገድ ትራንስፖርትና በተለይም በትልቁ የባቡር መንገድም ተሳስሯል። አሁን ደግሞ የተፈጥሮ ጋዝን በቧንቧ ከኦጋዴን ወደ ጂቡቲ ለማጓጓዝ ወደ ስራው ለመግባት እየተዘጋጁም ይገኛሉ። ይህ እንግዲህ የጂቡቲ ወደቡንና በመደራጀት ላይ ያለውን የታጁራን ወደብ የፈጠረው ሁለንተናዊ ትስስርን ሳይጨምር ነው። ይህ የኢኮኖሚ ውሕደት ብቻ ሳይሆን ጊዜ ጠብቆ ፖለቲካዊ ውሕደትንም ሊያመጣ እንደሚችል መሪዎቻችንም ደጋግመው ሲያነሱት ይሰማል። የጊዜ ጉዳይ እንጂ ሊሆን ይችላል። ታዲያ ይህ ሁሉ ሁኔታ ሊፈጠር የቻለው ታስቦበትና ይሆናል ተብሎ ቀደም ብሎ ታቅዶ ሳይሆን በኤርትራ ኪሳራና በኤርትራ መንግስት ያካሄድ የተሳሳተ ስልት ይመስላል። ከዚህ ዓይነቱ የተሳሳተ ስልት ያሁኑ የኤርትራ መንግስት ፈጠን ብሎ ለማስተካከል ካልሞከረ ደግሞ ጉዳቱ ላሁኑ የኤርትራ ትውልድ ብቻ ሳይሆን ለቀጣዩ ትውልድ እንዳይተላለፍም ያሰጋል። የኤርትራ መንግስት ሊገነዘበው የሚያስፈልገው ጉዳይ ቢኖር ኢትዮጵያ ያለ ኤርትራ ወደቦች ለመኖርና የቤት ስራዋን ለመስራት የምትችል መሆኗን ነው። ይህ ሁኔታ ባለፉት 20 ዓመታት በተግባር ተረጋግጧል። ስለዚህ የኤርትራ መንግስት ኢትዮጵያ ምጽዋንና ዓሰብን ካላገኘች ሕልውናዋ አደጋ ላይ ይወድቃል፣ ወይም ኢትዮጵያ ወደደችም ጠላችም እነዚህን ወደቦች ለመጠቀም ኤርትራን መለማመጧ ወይም መማጸኗ አይቀርም የሚል አስተሳሰብ ካለው አሁኑኑ ሊያርመውና ሊያስተካክለው ይገባል።

## 5.3. <u>ኢትዮጵያ፣ ሶማሊላንድና ኤርትራ፣</u>

በባብኤል ማንዴብና በኤደን ባህረ ሰላጤ አካባቢ እየታየ ያለው አዲሱ ክስተት ደግሞ የበርበራ ወደብ ጉዳይ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተቀማጭነቱ በተባበሩት ዓረብ ኤሚሬት የሆነው ቢ. ፒ. ዎርልድ የተባለ የወደቦች አልሚ ድርጅት የበርበራን ወደብ ለማልማት በማቀድ ከሶማሊላንድ አስተዳደር ጋር ውይይት ሲያደርግ ከቆየ በኃላ የለማውን ወደብ 51% ድርሻ ደ.ፒ. ዎርልድ የሚሆነውን ባለቤት ሲሆን፣ 31% የሶማሊላንድ አስተዳደር የሚይዝ ሆኖ፣ 19% ደግሞ የኢትዮጵያ መንግስት ድርሻ እንደሚሆን ተደርጎ ከስምምነት ላይ ተደርሷል። (ሳይሞን አሊሰን፣ 2018)

ኢትዮጵያ በበርበራ ወደብ ላይ ከላይ የተጠቀሰውን ድርሻ በመውሰድ ወደቡን ለማልማት ስትዘጋጅ ከኪሷ ገንዘብ አውጥታ ለማልማት የተዘጋጀች መሆኗን ያመላክታል። ይህም ድርጊት ኢትዮጵያ የወደብ ፍላጎቷን ከእድገቷ አንጻር በመመዘን ምን ያህል ባካባቢዋ ወደቦች ላይ ተጽእኖዋን ለማሳየት በመሞከር ላይ እንደምትገኝ ያመላክታል። ኢትዮጵያ በበርበራ ላይ ሀብት አፍስሳ ካለማችውና መጠቀም ከጀመረች በኃላ ጥቅሟን ለማስከበር ማንኛውንም ዓይነት የፀጥታና የመከላከል እርምጃ መውሰድ እንደምትችልም አመላካች እንቅስቃሴ ነው። ለምሳሌ በበርበራ ላይ የሶማሊያ መንግስትም ይሁን የሌሎች ኃይላት የተለየ ጣልቃ ገብነትና የማደናቀፍ ድርጊት ለመውሰድ የሚንቀሳቀሱ ከሆነ እጇን አጣጥፋ ትቀመጣለች ተብሎ እንደማይታሰብ የሚያሳይ ነው። በርግጥ ነው የጂቡቲ የሰላምና የጸጥታ ሁኔታም በማንኛውንም መልኩ እንዲደፈርስ ኢትዮጵያ እንደማትፈቅድም በርካታ ምክንያቶች መደርደር ይቻላል። ነገር ግን ባሁኑ ወቅት በበርበራ ወደብ ማልማት ላይ የወሰደችው እርምጃ ከሞቃዲሾው የሶማሊያ መንግስት ከልአላዊነት ጋር በተያያዘ አንዳንድ ተቃውመዎች እየተነሱበት እንዳሉም እየተሰማ ይገኛል። ሆኖም ሶማሊያ ራሷ የውስጥ ችግሯን በራሷ ፖለቲካዊ እርምጃዎች ማስተካከል ሲገባት ከ<<ሶማሊላንድ ጋር የልማት ስራ ማካሄድ አትችሉም!>> በሚል እሳቤ የኢትዮጵያን የልማትና የእድገት ፍላጎትን ለማደናቀፍ በቂ ምክንያት ስላልሆነ የሞቃዲሾው ተቃውሞ ብዙም እርምጃ ለመሄድ የሚችል አይመስልም። የሞቃዲሾው መንግስት <<ሶማሊላንድ መልማት የለባትም! መልማትዋንም ለመደገፍ ማንም ያካባቢ መንግስትም ይሁን ድርጅት መንቀሳቀስ አይችልም!>> ብሎ ለመወሰንና ለማደናቀፍም አይቻለውም። የዚህ ዓይነቱ ተቃውሞ ትርጉም የለሽና ተራ የጎረቤት ምቀኝነት ከመሆን የሚያልፍ እንቅስቃሴ ከመሆንም አያልፍም።

በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ በበርበራ ወደብ እየተጠናከረች መሄድ ለኤርትራው መንግስት ሌላው የማስጠንቀቅያ ደወል ተደርጎ ቢወሰድ ይበጀዋል። ኢትዮጵያ ከጂቡቲ ቀጥላ በበርበራ ወደብ የመጠናከርና እንደባለድርሻም አካል ሆና የመንቀሳቀሷ ጉዳይ የኤርትራ ወደቦች ለወደፊቱ በኢትዮጵያ በኩል ጥቅም ላይ የመዋል እድል እጅጉን እየጠበበ በመቀጠል ላይ መሆኑን ሊገነዘብ ይገባል። ያሁኑ ዓለም የጥቅምና የሰጥቶ መቀበል ዓለም

ነው እንጂ <<እሱ ካልጠየቀኝ፣ ካልለመነኝ ወዘተ…>> የሚል አቋም በመያዝ ጊዜ ሲያልፍ እያዩ እጅን አጣጥፎ መቀመጥ የሚያመጣው አንዳችም ጥቅም አይኖርም። ኢትዮጵያ እንደሆነች ከኤርትራ መንግስት የሆነ የግንኙነት ለውጥ ለማየት ካልቻለች፣ በጊዜ ሂደት የሞቃዲሾን፣ የቦሳሶን፣ የኪስማዩን፣ የሞምባሳን፣ የፖርት ሱዳንን ወደቦች ለመጠቀም የሚያስችላትን አካሄድ ልትከተል ትችላለች። በነዚህ ወደቦች ላይ የሚኖራት ድርሻና የተሻለ የመጠቀም አሰራር ከተመቻቸላት ደግሞ <<ምጽዋና ዓሰብ የሚባሉ ወደቦችም አሉና እስቲ እነሱን ልሞክር!>> ብላ ከኤርትራ መንግስት ጋር የምትለማመጥበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም። ስለሆነም የኤርትራ መንግስት ጊዜ ሳይወስድ አሁን ያለውን የተበላሸ ግንኙነትን ለመለወጥ የራሱን አንዳንድ አዎንታዊ እርምጃዎችን ከመውሰድ መቆጠብ አይኖርበትም። የኤርትራ መንግስትና ሕዝብ በወደቦቹ ምክንያት ተጠቃሚ የሚሆነው ወደቦቹ ለምተው ለወጪና ገቢ ንግድ የተመቻቹና አዋጪና ተወዳዳሪ ሲሆኑ ብቻ ነው እንጂ በወታደራዊ ኪራይና በወታደራዊ ካምፕነት ደረጃ የሚጠቅም ገቢ ሊያስገኙ እንደማይችሉ ማጤን ያስፈልገዋል።

## 5.4. <u>**የተባበሩት ዓረብ ኤሚሬት፣ ኤርትራ፣ ኢትዮጵያና ሶማሊያ፣**</u>

በሌላ በኩል ደግሞ የተባበሩት ዓረብ ኤሚሬት ከሳዑዲ ዓረብያና ከሌሎች መንግስታት ጋር ሆና በየመን ላይ ለምታካሂደው ዘመቻ እንዲረዳት ብላ ከኤርትራ መንግስት ጋር በፈጸመችው ወታደራዊ ውል መሰረት በዓሰብና አካባቢው ለፈጣን ወታደራዊ አውሮፕላኖች፣ ሄሊኮፕተሮች፣ ወታደራዊ ጀልባዎች ወዘተ.. የሚሆን ካምፕ በማቋቋም ላይ እንደምትገኝ ይነገራል።(አዳማኚ፣ 2016) ከዚሁ በተጨማሪም በዋሽንግተን ዲሲ የሚታተም Middle East Institute በሚባል እትም ኤሌኖራ አደማኚ የምትባል ፀሐፊ ባወጣችው ጽሑፍ የሚከተለውን ብላለች።

The Horn of Africa is currently playing a pivotal role in the U.A.E.’s security interests at a time of International uncertainty, regional conflicts, and demanding domestic transformations. The U.A.E. is expanding its foothold in the region, with Eritrea to host its first military base abroad and another in Somaliland in the works. Abu Dhabi’s ‘pivot in the Horn’ strategy is designed to tackle three rising security concerns now: Yemen’s instability, freedom of navigation threats, and piracy.(ዝኒ ከማሁ)

እንግዲህ የተባበሩት አረብ ኤሚሬት በየመን ባለው አለመረጋጋትና ውጊያ ምክንያት፣ በመርከቦች ነጻ እንቅስቃሴ ላይ ባለው ችግርና የባህር ውንብድናን መሰረት በማድረግ መብቴን አስከብራለሁ በማለት በኤርትራና በሶማሊላንድ ላይ የጦር ሰፈርን ለመመስረት ያካሄደችውን እንቅስቃሴ ምን ዓይነት የፀጥታና የወታደራዊ ተጽእኖ ባካባቢው አገራት ላይ ሊያስከትል ይችላል? የሚለው ጥያቄ እንዲሁ በቀላሉ ሊታለፍ የሚችል እንዳልሆነ መገንዘብ እንችላለን። ጉዳዩ በአገራችን በኢትዮጵያ ላይ ሊኖረው የሚችለው ተጽእኖስ ምን መልክ ሊኖረው ይችላል የሚለውም አሳሳቢ እንደሆነ መገመቱ አያዳግትም። ፀሐፊዋ በመቀጠልም የሚከተለውን መረጃም አስፍራለች።

In 2016, the Emirates opened a military base at Assab in Eritrea which encompasses an airbase, a deep-water port and a facility for military training. Following meetings between Eritrean President Isaias Afeworki and Saudi King Salman in April and December 2015, Eritrea permitted the use of its military bases to the Gulf states. A 30 year lease agreement between the U.A.E. and Eritrea is part of the aforementioned framework deal. In return the Gulf monarchies pledged a foreign aid package, which includes more fuel supplies to Asmara, the modernization of its international airport, and new infrastructure projects. The Emirates is now seeking to establish another naval outpost in the area in the unrecognized state of

Somaliland, at the town of Berbera. Somaliland’s parliament has approved the project, but it has to obtain the greenlight from Moqudishu to proceed, with objections also from Ethiopia and Djibouti. (ዝኒ ከማሁ፥)

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የተባበሩት ዓረብ ኢሜሬት የዓሰብን ወደብ ለወታደራዊ እንቅስቃሴ ለመጠቀም ለ30 ዓመት የሚቆይ የኪራይ ውል ከኤርትራው ፕሬዚዳንት አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ጋር እንደተዋዋለች የሚታወቅ ሆኖ በበርበራ ወደብም ተመሳሳይ ወታደራዊ ካምፕ ለመመስረት የተንቀሳቀሰች ብትሆንም ከኢትዮጵያና ከጂቡቲ በኩል ተቃውሞ የተሰነዘረባት ሲሆን የሞቃዲሾው መንግስት ይሁንታም ገና አላገኘችም። ነገር ግን ፍላጎቷ ሰማይ የነካና ባካባቢው ከፍተኛ ተጽእኖ ለማሳደር እየተንቀሳቀሰች እንደምትገኝ ግን እሙን ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የተባበሩት ዓረብ ኤሚሬት ንብረት የሆነው ዲፒ ዎርልድ የተባለ ዓለም አቀፍ የወደቦች አስተዳዳሪ ድርጅት ከጂቡቲ መንግስት ጋር ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የዶራህሌ ወደብን ለማስተዳደር ለ30 ዓመታት የሚቆይ ውል የተዋዋለ ሲሆን በሂደት ሲታይ ግን <<ይህ ድርጅት የጂቡቲ መንግስትን ሉዓላዊነትን ይዳፈራል>> በሚል ምክንያት ውሉን በብቸኝነት ለመሰረዝ የተገደደ ሲሆን ባንጻሩ ደግሞ ድርጅቱ ይህ ድርጊትን በመቃወም <<የጂቡቲ መንግስት ድርጊትን በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ዘንድ እቃወማለሁ!>> በማለት እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። የጂቡቲ መንግስት እንደዋዛ ላንድ ነጋዴ ድርጅት የሰጠው የወደብ የኪራይ ውል ምን ያህል ሉዓላዊነቱን እንደተዳፈረበት ባሁኑ ሰዓት ቢገነዘብም ከዚሁ በባሰ ሁኔታ የተለያዩ ኃያላን አገራት ደግሞ በኪራይ መልክ ያገሪቱን መሬት እየሸነሸኑና እየቦረቦሩ ወታደራዊ ካምፖችን ሰርተው ከሰፈሩና ከተደራጁ በኃላ ሉዓላዊነቱ በሆነ መንገድ ከስጋት ውስጥ ቢገባበት በምን ዘዴ ውሉን ሊያቋርጥባቸውና ሊያስወጣቸው እንደሚችል ደግሞ አንድ ፈጣሪ ብቻ ነው የሚያውቀው እንጂ የጂቡቲ መንግስት የሚያውቀው አይመስልም።

ኢትዮጵያ የጂቡቲ ወደቦች ሁነኛዋ ተጠቃሚና ተስተናጋጅ ከመሆኗ አንጻር ሲታይ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው አገራት በሆነ መንገድ ቢጣሉ ወይም ቢጋጩ ወይም ቢሳሳቡ በጥቅሜ ላይ አደጋ ሊያስከትሉ ይችላሉ ብላ በማሰብ የወሰደችው እርምጃ ያለ አይመስልም። ይህንኑ ስጋትን በቅጡ የሚያስተናግድ እቅድ ኢትዮጵያ ካላት በጣም የሚያስመግናት ሆኖ ባንጻሩ ደግሞ <<ምንም አይመጣብኝም!>> ብላ ተኝታበት ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ ምን ያህል አደገኛ መሆኑን ማስተዋል የግድ ይላል።

በሌላ በኩል ግን ኤርትራ የዓሰብ ወደብን ለውጭ ኃይሎች ወታደራዊ ካምፕነት ለረጅም ዓመታት በማከራየት ላይ በምትገኝበት ባሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ መንግስት የነዚያ ወደቦች በወታደራዊ ካምፕነት መደራጀት <<ለወደፊቱ አደጋ ይኖረዋል!>> ብላ በማስላት የሆነ ተዋቅሞ ለማሰማት አለመሞከሯም ሌላው ግብዝ አካሄድ ይመስላል። ቢያንስ ቢያንስ ተቃውሞ ማስነሳት ለነዚያ ካምፕ ፈላጊ አገራት ደወል ማሰማት ስለሚሆን ካንዴም ሁለቴ እንዲያመዛዝኑና አካሄዳቸውን እንዲያስተካክሉ ሊያደርጋቸው ይችላል። እንዲያው ሰምተው እንዳልሰሙ ዝም ማለት ግን ፖለቲካዊም ይሁን ዲፕሎማሲያዊም አይደለም።

## 5.5. <u>ግብጽና ቀይ ባህር፥</u>

የግብጽ መንግስት ደግሞ በምጽዋ አካባቢ የራሱን ወታደራዊ ካምፕ ለማቋቋም እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ይነገራል።(ስቴፋን ጎቼ፥ 2016) ለነገሩ ግብጽ የስዊዝ ካናል ባለቤትና ተቆጣጣሪ ስለሆነች በቀይ ባህርና ባካባቢው ለሚኖረው እንቅስቃሴ መደራደሪያ መረቧ ሰፊ ስለሆነ ብዙም ላትቸገር ትችላለች። ነገር ግን ከናይል ወንዝ ጋር በተያያዘ ሊመጣብኝ ይችላል የምትለውን ማንኛውንም ተጽእኖ ለመቋቋምና ለመጋፈጥ ግን እጇን አጣምራ የምትቀመጥ አገር አይደለችም። እንዲያውም ኢትዮጵያ የምትገነባው የህዳሴው ግድብ በህልውናዋ ላይ እንደ አንድ ሳንካ አድርጋ የምትወስደው ስለሆነ በዚህ ግድብ ላይ ልታደርሰው የምትችል እንቅፋት ካገኘሁ ብላ ደጋግማ የምታስብበት ጉዳይ እንደሆነ ያደባባይ ሚስጢር ነው። ምንም እንኳን ወታደራዊ ኃይል ተጠቅማ የግድቡን ስራ ለማስቆም ወይም ለማደናቀፍ ባትሞክርም ለዚሁ የማደናቀፍ ግብ የሚያደርስላት ማንኛውም አጋጣሚን ከመጠቀም ግን ቸል የምትል አይደለችም። ሆኖም በወታደራዊ ኃይል እንዳትጠቀም የዓለም ውግዘት የሚያደርስባት ከመሆኑም በላይ የራሷም ግዛት በተለይም እንደአስዋን ግድብ የመሳሰሉት ለኢትዮጵያ

ወታደራዊ ኃይል ዒላማ የመሆን እድላቸው ከፍ ያለ ስለሆነ የወታደራዊ እርምጃ አማራጭን እንደ ስልት ለመጠቀም ያስቸግራታል። ኢትዮጵያ በሕዝቧና በራሷ አቅም የምትሰራውን ግድብ በግብጽ አማካይነት ጉዳት ቢደርስበት ኢትዮጵያ በምንም ተዓምር አርፋ እንደማትቀመጥና ከፍተኛ ጉዳት ልታደርስባት እንደምትችልም ስለምታውቅ ይህንን የኃይል አማራጭ ለመጠቀም የምትፈልግ አይመስልም።

በሌላ በኩል ደግሞ ግብጽ የኢትዮጵያንና የኤርትራን ግጭትና በጠላትነት የመቀጠል ሁኔታን አጥብቃ የምትፈልገውና ልትጠቀምበት የምትመኘው እውነታ ስለሆነ ይህንን ዘዴ እንዴት አድርጋ ለጥቅሟ እንደምታውለው ማሰላሰሏ አይቀሬ ነው። የባድመው ጦርነትና ግጭት የግብጽ ስሪት የሆኑና በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ፀረ ሰውና ፀረ ተሽከርካሪ ፈንጂዎች ለኤርትራ መንግስት ተላልፎ በስራ ላይ እንደዋለ የትናንቱ ትዝታ ሆኖ አሁንም ቢሆን የኤርትራ መንግስት ኢትዮጵያን የመነካካቱ ተግባር አደጋ መሆኑን ስለተገነዘበና የግብጽን ፍላጎት ለማሟላት ስለማይችል ነው እንጂ የሆነ ግጭት በሁለቱ አገራት መካከል ለመቀስቀስ ቢችል ግብጽ በጣም የምትፈልገው ጉዳይ እንደሆነ ግልጽ ነው። ከዚህ በመለስ ግን የሁለቱ አገራት አለመግባባት ቀጣይ እንዲሆን በማድረጉ ስራ ላይ አሁንም ቢሆን ግብጽ እለታዊ ስራዋ መሆኑን መርሳት አይገባም።

ግብጽ ከሱዳን ጋር ያላት ግንኙነት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየተበላሸ እንደመጣ ይታወቃል። ሁለቱ አገራት ከመሐመድ ሙርሲው የወንድማማቾች መንግስት መገርሰስና ከአልሲሲ ወደ ስልጣን መምጣት ጋር በተያያዘ እየተበላሸና እየተጣመመ መጥቷል። የዚህ ዓይነቱ የተበላሸ ግንኙነት ለግብጽ መንግስት እረፍት የሚሰጠው ሆኖ አልተገኘም። የሱዳን መንግስት የሃላይብ ትሪያንግልን በግብጽ ወታደሮች ከተያዘና በጉልበት ካጣበት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በግብጽ መንግስት ላይ እምነት አጥቷል። የግብጽ መንግስት ጉልበት በመጠቀም የመከራከሪያ ቦታውን በመያዙ ምክንያት አመጸኛ መሆኑን አስመስክሯል። ስለሆነም ኢትዮጵያ የምትገነባውን የሕዳሴ ግድብ በሱዳን ጥቅም ላይ ምንም ጉዳት የማያደርስና ይልቁንም ለመስኖ ስራ የሚኖረው ጠቀሜታንና ጎርፍን በመከላከልም የሚጠቅም መሆኑን በመገንዘቡ ምክንያት ከግብጽ ጋር የነበረውን ታሪካዊ ግንኙነትን እርግፍ አድርጎ በመተው የሱዳን መንግስት ስለሕዳሴው ግድብ ጠቀሜታን በመጥቀስ የሚከራከር መንግስት ሆኖ ይገኛል። ይህ የሱዳን መንግስት የአቋም ለውጥ ለኢትዮጵያ መንግስት ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ሱዳን ከመሐል ላይ እያለች ደግሞ ግብጽ የሱዳንን መሬት ተጠቅሞ በኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ላይ ጉዳት ለማድረስ በጣም ያስቸግሯል። ስለሆነም ኢትዮጵያን ለመተናኮል ግብጽ በቅርብ ርቀት ሊጠቀምባት የሚችለው አገር ኤርትራ ብቻ ሆና ትታያለች። ስለሆነም የግብጽ መንግስት አንዳንዴ በኢትዮጵያ ላይ ጫና ለማድረስ ሲያምረው ኤርትራን ለመጠቀም እንደሚችል ለማሳየት ወይም የኤርትራን መሬት እንደሚጠቀም ለማስመሰል አንዳንድ ዲፕሎማሲያዊ ተግባራትን ሲጠቀም ይታያል። ሆኖም ይህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ለግብጽም ይሁን ለኤርትራ በዘላቂነት የሚጠቅማቸው አይሆንም። ይልቁንም የዚህ ዓይነቱ እሳት ከመጠቀም የናይል ውኃን ለጋራ ጠቀሜታ ለማዋል የሰጥቶ መቀበል ዲፕሎማሲን መከተሉ ሳይጠቅም አይቀርም።

ሱዳን ከግብጽ ጋር ባላት አተካሮ ምክንያት የቅርብ ርቀት ወዳጆችን እየሳበች ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዋን በማጠናከር ላይ ትገኛለች። ከነዚህም አገራት መካከል እነቱርክና ኳታር ይገኙባቸዋል። ሱዓኪን የምትባለዋን የቀይ ባህር ደሴቷንና ወደቧን የሐጂ ዑምራ ተጓዦች መተላለፊያ እንድትሆን በማለት ከቱርክ ጋር ስምምነት ከማድረጓም በላይ በኳታር እርዳታ ደግሞ ወደቡን ለማልማት 4 ቢልዮን ዶላር ወጪ ተደርጎ ለተለያዩ ዘርፎች መጠቀሚያነት እንዲያገለግል አገራቱ ከስምምነት ላይ ደርሷል። ይህም የቱርክና የኳታር በሱዳን ላይ የሚያደርጉት መንዣበብ ግብጽን የሰላም እንቅልፍ ሊሰጣት አልቻለም። ሱዳንን የጓዳ ቤት አድርጎ እንደድሮው ጊዜ ወደፈለገችው አቅጣጫ የማዘር ተግባር ለግብጽ ከእጇ ያመለጣት ክስተት መሆኑን ሊዋጥላት አልቻለም። ስለሆነም ሱዳን ከነቱርክና ከነኳታር ጋር የምታደርገውን መቀራረብና መወራረስ ግብጽ የምትፈልገው ጉዳይ አይደለም። ምክንያቱም የዚህ ዓይነቱ መቀራረብ ባንድ በኩል ሱዳን ራሷን ችላ እንድትቆምና በግብጽ ላይ የነበራት ተጽእኖ የሚቀንስላት ስለሆነ አጠናክራ የምትቀጥልበት ሆኖ በሌላ በኩል ደግሞ እነዚያ የቅርብ ሩቅ አገራት በቀይ ባህርና በሱአኪን ደሴት ላይ የልማት ተግባርን ለማካሄድና የባህር ኃይል ካምፖችን ለማደራጀት መፈለጋቸውና መንቀሳቀሳቸው ለግብጽ ጸጥታ አደጋ ሊኖረው ይችላል በሚል እሳቤ እንቅስቃሴውን በተለያዩ ዘዴዎች እየተቃወመችው ትገኛለች። ለዚህም ይመስላል ግብጽ ሱዳንን ለማስፈራራትም ይሁን ለማስፈራራት በማሰብና ከኤርትራ በኩል ተጽእኖ ለማሳደር በማለም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኤርትራውን መሪ አቶ ኢሳያስን ወደ ካይሮ በመጥራት የተለየና ሞቅ ያለ አቀባበልና መስተንግዶ በማድረግ <<እኔም ብሆን ካርድ አለኝ!>> ለማለት የተንቀሳቀሰች ይመስላል። ይህም በመሆኑ ሱዳን ሁኔታውን በጥሞና በመከታተል ወዲያውኑ ወታደሮቿን ወደ ኤርትራ ድንበር በማስፈር ከአገሪቱ ጋር የነበራትን ግንኙነት ልታሻክረው ችላለች።

## 5.6. <u>ሳውዲ ዓረብያ፣ ኳታር፣ የገልፍ አገራትና የቀይ ባህር፣</u>

ትልቋና ሃብታሟ የዓረብ አገር ሳውዲ ዓረብያ በቀይ ባህርና በምስራቅ አፍሪቃ አካባቢ ሊኖራት የምትፈልገው ፖለቲካዊ ተጽእኖ ብሎም ጥቅም ከፍተኛ ነው። የየመን መንግስት የሺኣ ሃይማኖት ደጋፊዎች በሆኑት በሁቱ ኃይሎች እጅ እንዳይወድቅ ባላት ፍላጎት መሰረት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ያላትን ወታደራዊና ንዋያዊ ሃብት ተጠቅማ የመንን ለማንበርከክ ከፍተኛ ወታደራዊ ዘመቻ ከፍታ አገሪቱን ድባቅ አስገብታት ይታያል። ይህ ግቧን ለማሳካትም ሌሎች የገልፍ መንግስታትንም ከጎኗ ለማሰለፍ የቻለች ሲሆን ከዚሁ ይባስ ብሎም ገንዘብ የምትረጥባቸውንም ያካባቢውን አገራት ጭምር ከጎኗ እንዲሰለፉ ለማድረግ ስታስፈራራና ተጽእኖ ስታደርግ ከርማለች። እርጥባኑ እንዳይቀርብኝ ያለ የቅርብና የሩቅ መንግስት ሁሉ <<አለሁልሽ! አለሁልሽ!>> ሲል ስለመክረሙ በቅርበት ስንከታተለው የቆየነው ጉዳይ ነው። ግብጽ ዋናዋ አጋር ስትሆን፣ ቻድ፣ ጂቡቲ፣ ሶማሊያ፣ ኤርትራ፣ ወዘተ... <<ከጎንሽ ነን!>> ብሏል። ኢትዮጵያ ከማንም ተፋላሚ ጋራ መወገኑ አላስፈለጋትም። ሆኖም ሳውዲ የኢትዮጵያን አቋም በጥሩ ጎኑ ልታየው አልፈለገችም። እንዲያውም ይባስ ብሎ ኢትዮጵያን የቀጣች መስሏት ለስራ ብለው ወደ ሳውዲ ተሰደው የነበሩትን ከሶስት መቶ ሺሕ በላይ ስደተኞችን <<ለጸጥታዬ ያሰጉኛልና ዜጎችሽን በሶስት ወራት ውስጥ አስወጪልኝ! አለበለዚያ እስር ቤት ውስጥ አጉራቸዋለሁ!>> በማለት ኢትዮጵያን ባልተጠበቀ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ አጣብቂኝ ውስጥ ልታስገባት ሞክራለች። ይህ የሳውዲ ድርጊትም ለኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ ተግባርና ግንኙነት ትልቅ ትምህርት ሰጥቶ ያለፈ ይመስላል።

በወጣቱ ልዑል አልጋወራሽ መሐመድ ሳልማን የምትመራው ሳውዲ ዓረብያ በምስራቅ አፍሪቃ ሊኖራት የምትፈልገው ተጽእኖ ሰፊና ከፍተኛ ይመስላል። በመሆኑም በየመን ላይ የጀመረችውን ዘመቻ ለማጠናከር ብላ በጂቡቲ ውስጥ ወታደራዊ ካምፕን ለማደራጀት እንቅስቃሴ እንደምታደርግ ከላይ ተጠቅሷል። ኤርትራ ውስጥም በዓሰብ ወደብ በተባበሩት ዓረብ ኤሜሬት የሚደራጀውን ወታደራዊ ካምፕ የሳውዲ ዓረብያ ተቀጥላ ስራ መሆኑ ይታወቃል። በሶማሊያም የሆነ ተጽእኖ እንዲኖራት ገንዘቧን ትሰጣለች። ከግብጽ ጋር ያላት የሞቀ ግንኙነት ወደ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ትስስር እንዲጠናከር ከመፈለግ አኳያ ሳውዲ በአስር ቢልዮኖች ዶላር የሚገመት ድጋፍ ለግብጽ አበርክታለች። በቅርብ ጊዜ ማለትም የካቲት 2010 ዓ.ም የሳውዲው ልዑል ግብጽን ሲጎበኙ በሳይናይ በረሃ ደቡባዊ ክፍል በ10 ቢልዮን ዶላር ወጪ አንድ አዲስ ከተማን ለመገንባት ሳውዲ ዓረብያ መስማማቷን በመገናኛ ብዙሃን ሲነገር ሰምተናል። <<ግብጽን የነካ ሳውዲን የነካ!>> ተደርጎ እንደሚወሰድ ዓይነት ጥብቅ ግንኙነትን አዳብሯል። የአገራት ግንኙነት መጠናከር በበጎ ጎኑ የሚታይ ቢሆንም ካገር ጥቅም አንጻር ሲገመገም ግን አሉታዊ ጎኑ ምን ይሆን? ብሎ ማሰላሰሉ አስፈላጊ ነው።

ሳውዲ ዓረብያ የገልፍ መንግስታትን አስተባብራ ኳተር ተብላ የምትታወቀውን ትንሽዬ ግን ደግሞ ተሰሚነት ያላትን አገር፣ በዓረቦች መለኪያ የስልጡኖች አገር ተብላ የምትታወቀውንና የአልጀዚራ ባለቤት የሆነችውን አገር ለመቅጣትና ለማፈን ብላ በቅርብ ጊዜ የወሰደችው አፍራሽ እርምጃን ስንመለከት ደግሞ አገሪቱ ባካባቢዋ የጠላችውን አገር ለመጉዳት ከፈለገች ምን ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ እንደምትቃጣ ዓይነተኛ ማሳያ ድርጊት ሆኖ ይታያል። ኳታር የገልፍ ስድስቱ አገራት ክለብ አባልና ምናልባትም በማንኛውንም መለኪያ የሳውዲ ጠላት ለመሆን ፍላጎት ሊኖራት የማይችል ትንሽ አገር ስትሆን ሳውዲ ዓረብያ ግን ትልቅ አገር መሆኗ ብቻ ሳይሆን ከኳታር ጋር ልትጣላ ትችላለች ተብላ የማትገመት አገር ናት። ሌላው ይቅር ኳታር ሳውዲ ዓረብያ ባደራጀችው የፀረ የመን ቡድን አንዲት አባል ሆና ስትሳተፍ የነበረች አገር ብትሆንም ኳታር ሳትጠብቀውና ሳትዘጋጅበት ሳውዲ ዓረብያ ግን ከመቅጽበት ግብጽን፣ የተባበሩት ዓረብ ኤሚሬትንና ባሕረይንን አስተባብራ ዲፕሎማቲክ ግንኙነታቸውን ባንድ ጀምበር በማቋረጥና የአየር አድማሳቸውንም ጭምር ለአገሪቱ አውሮፕላኖች በመዝጋት በከባባ ውስጥ እንድትገባ በማድረግ ሊያፍኑዋትና ሊደፈጥጧት ተንቀሳቅሷል። በዚህ የሳውዲ ዓረብያ ድርጊት ያካባቢው አገራት ሊማሩበትና ሊጠነቀቁበት ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ ዜጎቿን እንድታስወጣ በሳውዲ ዓረብያ የተላለፈባት ውሳኔም የዚህ ዓይነቱ ድርጊት አንዱ ማሳያ ነበር። ሳውዲን አምኖ በዚህ አካባቢ ሰልፉን የሚያስተካክል አገር ካለ አንድ ቀን የኳታር ዓይነት እድል ሊገጥመው እንደሚችል መጠርጠሩና የራስ ሰልፍን ከዘላቂ ጥቅም ጋር እያያዙ ማስተካከል ተገቢ መሆኑንም የዲፕሎማሲ ብልጠትና ችሎታን የሚጠይቅ ይመስላል።

ኤርትራም ብትሆን ከዚህ ጊዜያዊ የሳውዲ ዓረብያ ክለብ ውስጥ ገብታ ዘላቂነት በሌለውና አንድ ቀን ኳታር ያጋጠማትን እድል ሊደርስባት እንደሚችል ተገንዝባ በታሪክ አጋጣሚ ከተጣላቻት ከኢትዮጵያ ጋር ተቀራርባ ዘላቂነት ወደሚገኝበት ወዳጅነት ተመልሳ እድገቷን ብታራምድ ይሻላታል እንጂ ይህ የፔትሮ ዶላር ፍርፋሪ

ጠቀሜታ አይኖረውምና አቋሟን ብታስተካክል የአርቆ አስተዋይነት መገለጫ ሊሆናት ይችላል። ከኳታር መማር የማይችል ያካባቢው አገር ካለ <<ይብላኝ ላንተ እንጂ እኔስ ጉድጓዴን ምሻለሁ!>> የሚለው አባባል ሊነገርለት ይገባል። ይህንን እውነታ ማመዛዘን የማይችል አገር ባካባቢው የሚገኝ ከሆነ ውሎ አድሮ ጉዳቱ ለራሱና ለራሱ ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው። ኤርትራ በየመን ጉዳይ ላይ ጣልቃ የሚያስገባ አንዳችም አሳማኝ ምክንያት የላትም። በመሆኑም አዋጪ ሰልፏን ካሁኑ ጀምሮ ብታስተካክል የሚጠቅማት ይሆናል። በጊዜያዊና እርባና በሌለው የፔትሮ ዶላር ጥቅም መነሻነት የወደፊቱን የኤርትራ ሕዝብንና የአገሪቱን እድልና ተስፋን ወጥመድ ውስጥ አስገብቶ መምራት የሚያዋጣ አይደለም።

## 5.7. <u>ቱርክና ኳታር፣</u>

ቱርክ የድሮዋ የዓረብ አገሮች ገዥ የነበረችና ታሪኳም ከዚሁ የቅኝ ተገዥነት ዳራ ጋር የሚያያዝ ስለመሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም። አንዳንዶቹ የዓረብ አገራት በወዳጅነት ሲመለከቷት ሌሎች ደግሞ በጥርጣሬ የሚመለከቷት አገር ናት። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቱርክ ከአውሮጳ ሕብረትና ከአሜሪካ ጋር የነበራት ግንኙነት እየተበላሸ በመሄዱ ምክንያት ወደ አፍሪካ አገራት ፊቷን ያዞረች ትመስላለች። ከቅርብ ዓመታት በፊት ከሶስትና አራት የማይበልጡ የነበሩት ኢምባሲዎቿ ባሁኑ ጊዜ ወደ 39 አካባቢ ደርሷል። በአፍሪቃ ቀንድ ያላት ትኩረት ደግሞ ከሁሉም በላይ ጠበቅና ሞቅ ያለ ሆኖ እየቀጠለ ነው። በሶማሊያ መቃዲሾ ውስጥ ኢምባሲዋን ከፍታ የምትሰራ ሁነኛዋ አገር ከመሆኗም በላይ በቅርቡም ትልቁን ወታደራዊ ማሰልጠኛ ካምፕ ሰርታ ለአገሪቱ መንግስት አስረክባለች። በርከት ያሉ ወታደራዊ አማካሪዎችም አሰፍራለች።

በቅርብ ጊዜ ማለትም በታሕሳስ 2010 ዓ.ም ቱርኩ ፕሬዚዳንት ኤርዶጋን ሱዳንን በጎበኙበት ወቅት ከአቻቸው ፕሬዚዳንት አልበሽር ጋር 13 ያህል የልማትና የንግድ ስምምነቶችን ለመፈጸም ችሏል። እነዚህም የዩኒቨርሲቲ፣ የኤየርፖርት፣ የኃይል ማመንጫ፣ የእህል ወፍጮዎች፣ ነጻ የወደብ ቀጣና፣ ወዘተ… ያካተቱና ግምታቸው 650 ሚልዮን ዶላር ቱርክ የምታበረክተው ኢንቨስትመንት ይሆናል። ከዚሁ በተጨማሪም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ቱርክ በቀይ ባህር ወደብ ስትከታተለውና ስታዳብረው የቆየችውን የሱአኪን ደሴትን ከሱዳን የተቸራት ሲሆን በዚህ ደሴት ላይ ቱርክ የሐጂ ዑምራ ተጓዥ አፍሪካዊያን የሚያርፉበትን ትልቅ ማስተናገጃ ከፍተኛ ወጪ አድርጋ እንድታለማው ተፈቅዶላታል። ይህ ደሴት ቱርክ ለወታደራዊ ጠቀሜታ ልታውለው እንደምትችል የሚገመት ሆኖ ይህ ከፖርት ሱዳን በአምሳ ኪሎሜትር ርቀት ወደ ደቡብ አቅጣጫ የሚገኘው ወደብ ቱርክ ለወታደራዊ ጠቀሜታ ልታውለው የምትንቀሳቀስ ከሆነ ለግብጽ የራስ ምታት እንደሚሆንባት ተገምቷል። (አሽራፍ ሻዝሊ፣ ጌቲ ኢሜጅስ)

ከዚሁ የቱርክና የሱዳን ግንኙነት ጋር በተያያዘ የኤርትራ መንግስትም በጉዳዩ ላይ የተለየ ፍላጎት እንዳለው በመምሰል በጥር ወር 2010 ዓ.ም ላይ አንዳንድ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ ተስተውሏል። የግብጹ ፕሬዚዳንት አልሲሲ የኤርትራውን አቻቸው ፕሬዚዳንት ኢሳያስን ወደ ካይሮ ጋብዘውና ልዩ አቀባበል ሲያደርጉላቸው ተስተውሏል። ይህ ድርጊት እንደተፈጸመ ወዲያውኑ የሱዳን መንግስት ደግሞ ከኤርትራ ጋር ያለውን ምስራቃዊው ድንበር የጸጥታ ስጋት አለብኝ በሚል ሰበብ ድንበሩን ሲዘጋና ከፍተኛ ቁጥር ያለው ወታደራዊ ኃይል ወደ አካባቢው አንቀሳቅሶ ሲየሰፍር ታይቷል። ምክንያቱም ሱዳን ከግብጽ ጋር የነበራትን የንግድ ግንኙነት ዘግታ ባለችበትና በሃላይብ ሰርጥ ላይ ባላት አለኝታነት በምትወዛገብበትና ከቱርክም ጋር ጠበቅ ያለ ግንኙነት በጀመረችበት ሰዓት የኤርትራው መሪ ከግብጽ መናገሻ ከተማ ተገኝተው ከአልሲሲ ጋር ሲሞዳሞዱ መከረማቸው ሱዳንን ስጋት ላይ ሊጥላት በመቻሉ ምክንያት በድንበሯ ላይ የጥንቃቄ እርምጃ መውሰዷ ላያስገርም ይችላል።

## 5.8. <u>እስራኤል፣</u>

እስራኤል በሰሜኑ የቀይ ባህር ጫፍ በኩል ከዚህ ዓለምአቀፋዊ መተላለፊያ ከሆነው አካባቢ የምትጋራው ጥቅም ስላላት ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይም ባካባቢው ጂኦ ፖለቲካ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ማድረግ የምትፈልግ አገር ናት። እንደ መርህ የቀይ ባህር አካባቢ በዓረቦች ተጽእኖ ስር ጠቅልሎ እንዲገባ አትፈልግም። ምክንያቱም <<ቀን ሲጥል ዓረቦች ሊነሱብኝ ይችላሉ!>> የሚል ስጋት ስላላት ባካባቢው በሚካሄድ ማንኛውንም እንቅስቃሴ ድምጽና ተሰሚነት እንዲኖራት ትፈልጋለች። እስራኤል በቆዳ ስፋት ትንሽ አገር ብትሆንም በጉልበት ግን ትልቅ

አገር ናት። ወታደራዊና ቴክኖሎጂያዊ አቅሟ ጠንካራና አስተማማኝ ነው። ሆኖም በእብሪት <<ማንም አይነካኝም!>> የሚል አቋም የሌላትና ምናልባት ከጎረቤቶቹ ጋር ግጭት ቢፈጠር መልሴና አዋጪ መንገዴ ምን መሆን አለበት በማለት እንቅልፍ ተኝታ ማደር የማትፈልግ ንቁ አገር ናት። በዚህ የቀይ ባህር አካባቢ አብዛኛው አገር ድብን ያለ እንቅልፍ የሚተኛበት ሰዓት ይኖረዋል ብለን ብንገምት ማንንም ባለማመን <<እንቅልፍ አያስፈልገኝም!>> ብላ በንቃት ድንበሯን የምትጠብቅ አገር ብትኖር እስራኤል ናት ብንል ማጋነን አይሆንም።

በ1980 ዓ.ም በደርግ መንግስት ፈቃድ ለኢንተሊጄንስ ስልጠና ከአንድ ቡድን ጋር ሆኘየ ወደ እስራኤል አገር የሄድኩበት አጋጣሚ ነበር። በዚህ የአንድ ወር ተኩል ጊዜ ስለ እስራኤላዊያን ያኗኗር ሕይወት ያስተዋልኩት ጉዳይ ቢኖር እስራኤላዊያን በጣም ንቁ ሕዝቦችና ብዙ ጊዜያቸውንም በእንቅልፍ ላይ የማያሳልፉ ሕዝቦች መሆናቸውን ነው። ለምሳሌ የኛን ቡድን እንዲያስተባብር ተመድቦ የነበረውና ምናልባትም እድሜው በ60ዎቹ አጋማሽ የሚሆነው ጡረተኛ ኮሎኔል በእረፍት ጊዜያችን ከኛ ጋር ሲኳትን ውሎ ሲያበቃ እኛን አስተኝቶ ለሌላ ሁለተኛ ስራው ይሄድና ገና እኛ ከእንቅልፍ ከመነሳታችን በፊት ካረፍንበት ቦታ መጥቶ በንቃት ከካፊተሪያው ቁርሱን ሲበላ እናገኘዋለን። ንቃቱ የሱ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ሕዝብ ይመስላል። ቀንና ሌሊት የሕዝቡ እንቅስቃሴ ብዙ ለውጥ አይታይበትም። ጉዳዩን ከእድገት ደረጃ ጋርና 24 ሰዓት ስራ የመስራቱን ሂደት ወይም ልምድ ሊያመላክት ይችላል። ይህ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ በእንቅልፍ ደረጃም ቢሆን ከመካከላችን ሰውየውን መቼና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚተኛ ጠይቀነው የሰጠን መልስ ከ2 እስከ 3 ሰዓት አካባቢ በየቀኑ እንደሚተኛ ወይም ሸለብ እንደሚያደርገው ገልጦልን ነበር። ታዲያ ይህ ሸለብታ በተመቸው ቦታ ሊሆን እንደሚችልና ጊዜ ወስዶ አልጋን አስተካክሎ የሚፈጸም እንቅልፍ እንዳልሆነ ግን በእርግጠኝነት ነግሮናል። ከሳሎን ወንበር ላይ ወይም በቢሮ አካባቢ ከሚገኝ ማረፊያ ቦታ ላይ ሊሆንም እንደሚችልም ይናገራል። እስራኤላዊያን ሕይወታቸው ይህን ይመስላል። የእስራኤል ጦር አባል አብዛኛው በመደበኛነት የተሰማራው ብቻ አይደለም። አብዛኛው በሌላ ስራ ላይ ተሰማርቶ የሚገኝና ሪዘርቭ ተብሎ የሚጠራው ነው። ሕዝቧ በተለይም አይሁዶቹ ከ4 ሚልዮን ስለማይበልጡ ከዚህ ሕዝብ መካከል ውሱኑን የሰው ኃይል ካልሆነ በስተቀር በመደበኛ ውትድርና ማሰለፍ የአገሪቱን የልማትና የእድገት ሂደትን የሚጎዳ ስለሆነ ይህንን ከግምት በማስገባት በጣም ጥቂት ሰው ብቻ ነው ሙሉ ጊዜውን በውትድርና ማሳለፍ የሚችለው። ነገር ግን እድሜው 18 ዓመት የደረሰው ወንድም ሴትም በውትድርና አገልግሎት እንዲያልፍ ሕጋዊ ግዴታ ስለሆነ አገልግሎቱ የጨረሰ ማንኛውም እስራኤላዊም በተጠራ ጊዜ በተመደበለት ቦታ እንዲገኝ ተደርጎ ስለተዋቀረ ሌላ ከአቅም በላይ የሆነ ነገር ካላጋጠመ በስተቀር ሁሉም በውትድርና ሰልጥኖ የወጣ ዜጋ ወታደር ነው ለማለት ይቻላል። ይህ ሕይወት የውዴታ ግዴታ ነው። እስራኤልን ከበው የሚገኙት አረቦች ከፍልስጤሙ ጥያቄ ጋር በተያያዘ የአገሪቱ ጠላቶች ተደርገው የሚወሰዱና ባጠቃላይ ሕዝብ ብዛትም እስከ 200 ሚልዮን የሚሆን ሕዝብ ያላቸው ስለሆኑ እስራኤል ላለመተኛት መወሰኗ ከህልውናዋ ጋር ተያያዥነት ያለው መሆኑን እንመለከታለን።

ስለሆነም እስራኤል አካባቢውን በቅርበትና በንቃት የምትጠብቅ አገር ናት። ሌላው ተኝቶ እንቅልፉን ሲለጥጥ እስራኤል ሌሊቱን ስትጓዝ አድራ በሆነ ጓዳ ጎድጓዳ ገብታ፣ የምታጠፋውን አጥፍታ፣ የምትወስደውን እርምጃ ወስዳ ስታበቃ አጥፊው ወይም እርምጃ ወሳጁ ማን እንደሆነ ሳይታወቅ ነገር ግን <<ይህችን ልታደርግ የምትችለው እስራኤል ናት!>> እየተባለች ከሐሜት ያላለፈ መረጃ ሳይገኝባት የፈለገችውን ውጥን አከናውና የምትኖር ብልጥና ንቁ አገር በመሆኗ እስራኤል በቀይ ባህር የሚከናወነውን ማንኛውንም ድርጊት በቅርበትና በጥንቃቄ የምትከታተል አገር መሆኗን መዘንጋት አይገባም። ባጠቃላይ ሲታይ እስራኤል የምትኖረው ሕይወትና የምትፈጽመው እንቅስቃሴ ያጓጓል፣ ያስቀናልም። ስለሆነም ባሁኑ ወቅት የዓረቦችና የኢራን መንግስታት በየመን ላይ የሚካሄዱትን ግጭትና ጣልቃ ገብነትን በአዎንታዊና በአሉታዊ ጎኑ የመከታተልን፣ የገልፍ ክለብ አባል መንግስታትና ግብጽ በኳታር ላይ የፈጸሙትን ያልተጠበቀ አፍኖ የማስቃየት ተግባርን፣ የኃያላን መንግስታት በጂቡቲ ወታደራዊ ሰፈር የማደራጀትን፣ የዓረቦች በሶማሊያ፣ በኤርትራና በጂቡቲ የሚያደርጉትን ወታደራዊ እንቅስቃሴ አንድምታን፣ የቱርክ በሱዳን ላይ የምታካሄደው አጠቃላይ እንቅስቃሴን፣ ግብጽ በኤርትራ ላይ የምትከተለውን ፖሊሲና ጣልቃ ገብነትን፣ ግብጽ ከናይል ጋር በተያያዘ ከኢትዮጵያ ጋር የምታካሂደውን አተካሮን፣ ወዘተ.. ሁሉ እስራኤል ከራሷ ጥቅም ጋር በማያያዝ በቅርበት ከምትከታተላቸው ጉዳዮች ጥቂቶቹና ዋንኛዎቹ ሊሆኑ እንደሚችሉ መገመትም ይቻላል።

ከላይ የተጠቀሰው በቀይ ባህር አካባቢ በዓረቦችና በሌሎችም አገራት የሚካሄደው ወታደራዊ እንቅስቃሴና አሰላለፍ በኢትዮጵያና በኤርትራ ላይ ለወደፊቱ ምን ዓይነት ጂኦ ፖሊቲካዊ ተጽእኖ ሊፈጥር ይችላል? ሁለቱን አገራት በመካከላቸውም ይሁን ከሌሎቹ ተዋናይ አገራት ጋር ወደ በለጠ ፍጥጫ ሊያስገባቸው የሚችል ሁኔታ

ሊከሰት ይችላል ወይ? ሁለቱም መንግስታት አሁን ባላቸው ፍጥጫ ከቀጠሉ ያከባቢውን ወቅታዊ ፖለቲካዊ አሰላለፍ አንዱ ሌላውን ለመጉዳት ሊጠቀሙበት ይችሉ ይሆን ወይ? ወዘተ… የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳቱ ተገቢ ይመስለኛል። ባሁኑ ወቅት ለጥያቄዎቹ መልስ መስጠት መሞከር ግምታዊ ከሚሆን በስተቀር በማስረጃ ላይ የተደገፈ አስተያየት ስለማይሆን ወደ ቀጣዩ ርእስ በቀጥታ ማለፍና ከርእሱ ጋር አያይዞ ስለመፍትሔ መንገዱን የመሻት ሂደት ግን ሊጠቅም ይችላል።

## 5.9. <u>ኢጋድና ቀይ ባህር፣</u>

የምስራቅ አፍሪቃ በይነ መንግስታት ወይም ኢጋድ አባል አገራት ለቀይ ባህር በጣም ቀረቤታ ያላቸውና ምናልባትም ባካባቢው ሊከሰት የሚችል ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ሊጎዳቸው ወይም ሊነካቸው የሚችል ነው። ኤርትራ፣ ሱዳን፣ ጂቡቲና ሶማሊያ ወይም ሶማሊላንድ የቀይ ባህር አጎራባች አገራት ሲሆኑ ሌሎቹ አባላትም ቢሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴያቸው ከቀይ ባህር ጋር የተቆራኘ ነው። ለምሳሌ የኢትዮጵያ 90% የወጪና የገቢ ንግድ እንቅስቃሴ የሚተላለፈው በቀይ ባህር በኩል ነው። እንደቡብ ሱዳን፣ ኬንያና ኡጋንዳም ቢሆኑ የንግድ እንቅስቃሴያቸው በቀይ ባህር ላይ የሚተላለፍ ነው። ስለሆነም በቀይ ባህር የሚደረግ ማንኛውንም ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ… እንቅስቃሴዎች የኢጋድ አባል አገራትን ጥቅም የሚነካ መሆኑ ግልጽ ነው። ነገር ግን ኢጋድ በጣም በሚገርም ሁኔታ በቀይ ባህር በመከናወን ላይ ባሉት የኃያላን መንግስታት እንቅስቃሴዎች ላይ አንዳችም አስተያየት ወይም ስጋት ሲያቀነቅን አይታይም። ኢጋድ ይቅርና ስለ ቀይ ባህር ሁኔታ ስጋቱን አስመልክቶ አስተያቱን ሊናገር ይባስ ብሎም ራሱ ኢጋድ አባል አገራቱን በቅጡ የማስተባበርና የማቀራረብ ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ ሲያደርግም አይታይም።

ለምሳሌ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ከተጋጨችበት ጊዜ ጀምሮ ኢጋድ ከኢትዮጵያ ጋር ወግኖ ኤርትራን ከማውገዝና ምናልባትም በአፍሪቃ ሕብረትና በተባበሩት መንግስታት እንድትወገዝና ማእቀብ እንዲደረግባት ከመወትወት ውጭ አገራቱን ለማቀራረብና ችግሮቻቸውን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ በማድረጉ አቅጣጫ ላይ አንዳችም እንቅስቃሴ ሲያደርግ አይታይም። ይህም ሁኔታ የኢጋድን ትልቅ የዲፕሎማሲና የፖለቲካ ግድፈት ከመሆን ሌላ ትርጉም ሊሰጠው የሚችል ጉዳይ አይደለም። ከኢጋድ ግድፈት ጋር በተያያዘ በዋናነት ተጠያቂ ልትሆን የሚገባት ኢትዮጵያ ናት። የኢጋድ ሊቀመንበር በመሆኗና ከዚሁ እልፍ ባለም ምንም እንኳን ከቀይ ባህር ጋር ባትዋሰንም የቀይ ባህርን መተላለፊያ ከነሳውዲና ከነሱዳን ባልተናነሰ ጥቅሟን ሊነካ የሚችል መሆኑ ግልጽ ቢሆንም ከራሷ ጥቅም አኳያና ከኢጋድ ኃላፊነት አንጻር ተገቢ ሚና መጫወት ሲኖርባት እንደማይመለከታት ተመስላ በዝምታ ብቻ ያከባቢውን ሁኔታ ለመከታተል መፍቀዷ ግራ የሚያጋባ ሆኖ ይታያል።

## 5.10. <u>የዲፕሎማሲው ጥረት፣</u>

ዲፕሎማሲ ሲባል የሁለቱንም አገራት ማለትም የኢትዮጵያንና የኤርትራን የሚመለከት የዲፕሎማሲ መንገድን ለመግለጽ ነው። ሁለቱም አገራት ከሌሎች መሰልና ግጭት ውስጥ ገብተው ችግራቸውን በዲፕሎማሲ ከፈቱ ወይም ለመፍታት ጥረት ካደረጉ መንግስታት ጋር አያይዞ ማስቀመጡና ማነጻጸሩ ተገቢ ይሆናል። እስካሁን ድረስ እንደታየው ሁለቱም አገራት ችግራቸውን ለመፍታት በዲፕሎማሲው መንገድ ተገቢ ጥረት አላደረጉም። ሁለቱም አገራት በሚያለያያቸው ላይ ትኩረት ከማድረግና አንዱ ሌላውን ለመጉዳት ጥረት ከማድረግ በስተቀር ቆም ብለው <<እስቲ ለዲፕሎማሲው መንገድ ወይም መፍትሔ አማራጩን እንፈልግለት>> ብለው ሲንቀሳቀሱ አልታዩም። ብዙውን ጊዜ እንዳየነው አንዱ አገር ሌላውን ለመጉዳት የሆነ እርምጃ ወይም እንቅስቃሴ ሲያደርግና ሌላኛው አገር ደግሞ <<በል እንግዲህ የኔ ምትና አጸፋ ደግሞ ምን እንደሚመስል ቅመሰው!>> የሚል ዓይነት ግብረ መልስ ሲሰጣጡ እንጂ በሰለጠነ መንገድ ወይም በዲፕሎማሲያዊ መንገድ <<እኔ ይህንን አድርጊልሃለሁ፣ ካንተ ደግሞ አዎንታዊ ግብረ መልስ እጠብቃለሁ፣ እኔ አንተን ለመርዳት ይህንን እርምጃ ወስጃለሁ፣ አንተ ደግሞ የኔን ቀና አመለካከትና እርምጃ ከግምት ውስጥ አስገብተህ ምን ለማድረግ እንደምትፈልግ አያለሁ፣ ወዘተ…>> የሚመስል ዲፕሎማሲያዊ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ አልታዩም።

ካለፉት ዓመታት አካሄዳቸው እንደምንገነዘበው ሁለቱም አገራት ለዲፕሎማሲው ሂደትና መፍትሄ ትኩረት አድርገው ሲንቀሳቀሱ አልታዩም። ከሁለቱም አገራት እርምጃ የምናየው ነገር አንዱ በሌላኛው ላይ ምን ያህል

ጎል እንዳስገባና <<ጉድ አደረግኩት፣ ሰራሁለት! ወዘተ…>> ዓይነት የሚመስል እንቅስቃሴ ሲያሳዩ ነው የከረሙት። ይህ ድርጊት ደግሞ የሌሎች ጎረቤት አገራት መሳቂያና መሳለቅያ ከመሆን በስተቀር ለአገሩቱ ዘላቂ ሰላምና የወደፊት የጋራ እድገት የሚበጅ አይደለም። በርግጥ ነው የኢትዮጵያ መንግስት ኤርትራዊያን ስደተኞችን በመቀበልና በተለያየ ዘርፍ በመርዳት ያደረገው አስተዋጽኦ ከላይ የጠቀስነው ጉዳይ ስለሆነ እዚህ ላይ መድገሙ ተገቢ አይሆንም። ነገር ግን በሁለቱም አገራት ኢምባሲዎች አካባቢ የጋራ ግንኙነትን በግልጽም በምስጢርም በመፍጠር ለዲፕሎማሲው እንቅስቃሴ የሚበጁ ተግባራት ሲከናወኑ አልታዩም። የሁለቱም አገራት ዲያስፖራን ዒላማ በማድረግ ለዲፕሎማሲው ግንኙነት ሊረዱ የሚችሉ ግልጽም ምስጢራዊም እንቅስቃሴዎች ሲካሄዱ አልታዩም። ስደተኞችን ዒላማ በማድረግ ከአገር ቤት ዘመዶቻቸውና ጓደኞቻቸው ጋር ግንኙነቶችን በመፍጠር የዲፕሎማሲውን ምሕዳር ለመጠቀም የሚረዱ ተግባራት ሲከናወኑ አልታዩም። የሁለቱንም አገራት ምሁራን /በተለይም ከውጭ የሚገኙትን/ መሰረት በማድረግ በሁለቱም አገራት የወደፊት ግንኙነትን አስመልክቶ ምን ማድረግ እንደሚበጅ የሚያመላክቱ እንቅስቃሴዎች ወይም ጥናቶች በጥሞና ሲካሄዱ አልታዩም፣ ወዘተ…። በዚህ ሂደት የተወሰነ እርምጃ ቢከድበት ኖሮ ለዲፕሎማሲው ተግባር በርካታ ጠቃሚ ውጤቶች ወይም አዎንታዊና ጠቋሚ መንገዶች ይታዩ ነበር። ይህ ባለመደረጉ ምክንያት ሂደቱ የጠፋ ጊዜ ነበር ከማለት ውጭ በሌላ ሁኔታ መፈረጅ የሚቻል አይመስለኝም።

በዚህ ርእስ ላይ እየተነጋገርን የምንገኘው የዲፕሎማሲውን ምሕዳር ሁለቱም አገራት ምን ያህል ተጠቅመውበታል? ምን ያህል ምሕዳሩን በመጠቀም ሰላማዊ መፍትሄ ለማምጣት ሞክሯል? ተነሳሽነቱን በመውሰድ የዲፕሎማሲውን ምሕዳር በጥንቃቄና በብልጠት ለመጠቀም ዋናውን ሚና መጫወት የነበረበት የትኛው አገር ነው? አንዱ አገር ተነሳሽነቱን ሲወስድ ሌላኛው አገርስ ምን ማድረግ ይጠበቅበት ነበር? ወዘተ… የመሳሰሉ ጉዳዮችን አንስተን ለመወያየት የሚረዳ ይመስለኛል።

1. በመሰረቱ ኤርትራ በኢትዮጵያ ውስጥ ህውከትና ብጥብጥ እንዲፈጠር ከፍተኛ ጥረት ስታደርግ መቆየቷ አሌ የማይባልና የታወቀ ጉዳይ ነው። ነገር ግን ኤርትራ በምስራቅ አፍሪካ ካሉት አገራት ከጂቡቲ ቀጥላ ትንሽዋ አገር ናት። የሕዝቧ ብዛትም ቢሆን ከስድስት ሚልዮን የሚበልጥ አይደለም። ነገር ግን የኤርትራ መንግስት ከእግሩ መጠን በላይ ጫማ ለማድረግ እንደሚሞክርም ይታወቃል። ባንጻሩ ደግሞ ኢትዮጵያ ባካባቢው ትልቅ አገር ብቻ ሳትሆን የአፍሪካ ሕብረት መቀመጫና በዓለም ውስጥ ከኒው ዮርክና ከለንደን ቀጥሎ ከፍተኛ የዲፕሎማቲክ ጽ/ቤቶች ያሏት አገር ናት። የኢትዮጵያ ጎረቤቶች አገራትን ማለትም የኬንያ፣ የሱዳን፣ የደቡብ ሱዳን፣ የሶማሊያ፣ የኤርትራና የጂቡቲ ሕዝብ ባጠቃላይ ተደምሮ ከኢትዮጵያ ሕዝብ በቁጥሩ ያንሳል። ባሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ወደ 102 ሚልዮን አካባቢ ደርሷል። ይህም የሚያሳየው ኢትዮጵያን ከኤርትራ ጋር በተለያዩ ንጽጽሮች ማወዳደሩ ተገቢ አይሆንም ለማለት ነው።
2. እንደሚታወቀው ሁለቱም አገራት በተለያዩ ዘዴዎች ማለትም በፖለቲካው፣ በዲፕሎማሲው፣ በኢኮኖሚው፣ በማሕበራዊው፣ በወታደራዊና በኢንተሊጀንሳዊ ተግባራት ሲጠቃቁ ከርሚል። በርግጥ አንዱ በሌላኛው ላይ የበለጠ ጉዳት አድርሶበታል በማለት ዝርዝሮችን ማቅረብ ይቻል ይሆናል። ነገር ግን ላሁኑ ጉዳያችን የሚጠቅም አይደለም። ጉዳት መድረሱ ብቻ መጥቀሱ በቂ ነው። ይህ ጉዳት እንዲቀርና ሁለቱም አገራት ወደ መደበኛው የዲፕሎማሲ ግንኙነት ገብተው ሰላማዊ ሁኔታ እንዲፈጥሩ ምን መደረግ አለበት? ወደሚለው ማተኮሩ ነው ሊበጅ የሚችለው።
3. ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ኤርትራ ትንሽ አገር በመሆኗና ኢትዮጵያ ደግሞ በተነጻጻሪ ትልቅ አገር በመሆኗ በሁለቱም አገራት መካከል በሚካሄድ መጠቃቃት በሌሎች ታዛቢ ወይም ተመልካች አገራት ዘንድ የሚታዘንላት አገር ማን ትሆናለች? ተብሎ ቢጠየቅ ኢትዮጵያ ናት የሚል መልስ ከየትም አቅጣጫ ማግኘት እንደሚከብድ የታወቀ ነው። ለምን ቢባል ኤርትራ አሁንም ትንሽ አገር በመሆኗ ከፍተኛ ጥፋት የተፈጸመው በርሷ መሆኑ ከበድ ያለ ማስረጃ ይቅረብ ብለን ብንገምትም ኤርትራ ናት አጥቂዋ ብሎ የሚቀበል አገር ግን ብዙም አይኖርም። <<እንዴት ትንሽ አገር ትልቅ አገርን ለመጉዳት ትችላለች?>> የሚል ጥያቄ በማንሳት ነው ኢትዮጵያን አጥቂ አድርጎ ለማስቀመጥ የሚሞከረው። ለምሳሌ ባውሮፓ በተለይም የስካንዴነቪያን አገራትና የአውሮጳ ሕብረት አባል አገራት በሙሉ (ከጥቂቶቹ በስተቀር)፣ እነጣሊያን፣ እነስሎቬንያ፣ ክሮኤሽያ፣ ሞንተኔግሮ፣ መቄደንያ፣ ወዘተ… የመሳሰሉት አገራት የኤርትራ ነባር ደጋፊዎች ሆነው የኖሩና አሁንም ቢሆን ኢትዮጵያን አጥቂ አድርገው ከመፈረጅ የማይመለሱ አገራት ናቸው። ለምን ቢባል ይህ ሁኔታ በተለይም የስካንደነቪያን አገራትን ብንወስድ ከትጥቅ ትግሉ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የዘለቀና አንዳንዶቹም ትናንሽ አገራት በመሆናቸው ኤርትራን አጥቂ አድርገው ለመውሰድ የሚቸገሩ ናቸው። በአረቡ ዓለምና በሌሎችም አህጉር የሚገኙ ትናንሽ አገራትም ቢሆኑ ከላይ ከተጠቀሰው

አቋም የተለየ አቋም ለመያዝ ይከብዳቸዋል። በነገራችን ላይ ኤርትራ የአረብ ሊግ ታዛቢ አባል አገር መሆኗንም መዘንጋት የለበትም። ለማንኛውም እዚህ ላይ ደጋፊና ተቃዋሚ አገር በመፈረጅ ለጉዳዩ ውጤታማነት ተገቢነት ይኖረዋል ለማለት ሳይሆን ኢትዮጵያ ትልቅ አገር በመሆኗ <<በኤርትራ ተጠቃች!>> የሚለውን አባባል ለምን ተቀባይነት ሊያጣ እንደሚችል ለመጠቋቆም ብቻ ነው።

4. በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ስለመሆኗና በዓለም መድረክ ተሰሚነቷ እየተጠናከረ በመምጣቱ ምክንያት በተባበሩት መንግስታት ለፀጥታው ምክር ቤት ተለዋጭ አባልነት ከ190 ተሳታፊ አገራት የ185 ድጋፍ አግኝታ ከጀንዋሪ 01/2017 ጀምሮ ወንበሯን ለመያዝ ችላለች። ድጋፍ የነፈጉዋት አምስቱ አገራት ኤርትራ፣ ግብጽ፣ ሳውዲ አረብያ፣ ኳታርና ሴኔጋል ብቻ ነበሩ። እያንዳንዱ አገር የየራሱ ምክንያት ይኖረዋል። ይህ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ ከፍተኛ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሰላም አስከባሪ ኃይል ለማሰማራት የበቃች አገር ናት። ለምን ቢባል በሰላም አስከባሪው ኃይል ብቃትና ዲስፕሊን ምክንያት ተመራጭ ወታደራዊ ኃይል የምታሰማራ አገር ሆና በመገኘቷ ነው። ስለሆነም ኢትዮጵያ ባሁኑ ጊዜ ከኤርትራ ጋር በትንሹም በትልቁም ጉዳይ እንካ ስላንቲያ እየገባች ለመቀጠል መሞከር ያለባት አይመስልም። ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር እየተነታረከች መኖሯም አይምርላትም፣ አይበጃትምም። ለኢትዮጵያም የተባበሩት መንግስታቱ የፀጥታው ምክር ቤት መድረክ ከኃያላኑ አገራትና ከመሰል አባል አገራት ጋር በቀላሉ የሚያገናኛት በመሆኑ መድረኩን ከኤርትራ ጋር ላላት የሻከረ ግንኙነትንም ለመለወጥ የምትጠቀምበት መሆን ይኖርበታል። ስለሆነም ለዲፕሎማቲክ ግንኙነቱ ተነሳሽነቱን ወስዳ መንቀሳቀስ የሚኖርባት አገር ኢትዮጵያ ናት።

5. አንዱና በቅድሚያ ኢትዮጵያ ልትገነዘበው የሚገባው ጉዳይ የኤርትራ መንግስት ባንድ ወቅት በራሱ መንገድ ይወድቃል ብላ ከመጠበቅ ይልቅ አሁን በስልጣን ላይ ካለው የኤርትራ መንግስት ጋር በጉርብትና በሰላም ለመኖር የዲፕሎማሲ ጥረቷን መቀጠል ይኖርባታል። ኢትዮጵያ ከምስራቅ አፍሪካ በይነ መንግስታት ጀምራ ኤርትራ ወደ ክፍለ አህጉሩ ድርጅት እንድትመለስ የራሷንና የአባላቱን ተሳትፎ ተጠቅማ እንቅስቃሴ ብታደርግ በኤርትራ መንግስት ዘንድ ጥሩ የዲፕሎማቲክ እይታ /ዲፕሎማቲክ ጀስቸር/ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ኤርትራ ወደ በይነ መንግስታቱ ድርጅት /ኢጋድ/ እንድትመለስ አሁንም ከተባበሩት መንግስታት ዘንድ <<ከዕዳ ነፃ መሆንሽን የሚያረጋግጥ ሰነድ ይዘሽ ቅረቢ /Clearance/>> መባሏ ትክክለኛ የዲፕሎማሲ ጥረት እንደተደረገ የሚያሳይ አካሄድ አይመስልም። የክፍለ አህጉሩ ድርጅት አባል አገራቱ እርስ በርሳቸው የሚረዳዱበትና የሚተጋገዙበት እንጂ ሌላ የተለየ ዓላማ ያለው አይደለም። ስለሆነም አንዱ አገር ሌላውን ለማጥቃት ወይም ለመጉዳት የሚጠቀሙበት መሳሪያ ተደርጎ መወሰድ ያለበት አይደለም። ስለሆነም ኤርትራ ወደ ክፍለ አህጉሩ ድርጅት ለመግባት የማንም አገር ድጋፍ ወይም ተቃውሞ ሊቀርብባት አይገባም። ኢጋድ ድርጅቷ ነው፣ ስለሆነም ተመልሳ የመግባት መብቷ በማናቸውም ዓይነት ቅድመ ሁኔታ ሊታገድ ወይም ሊዘጋ አይገባም። ኤርትራ ወደ ክፍለ አህጉር ድርጅቱ ብትገባ ደግሞ ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ችግር ብቻ ሳይሆን ከጅቡቲና ከሌሎችም አገራት ያላትን ግንኙነት በዲፕሎማሲው መንገድ ለመፍታት ከቅርብ ትገኛለች፣ ሁኔታዎች ሁሉም አገራት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር ይጠቀሙበታል። ታዲያ ኤርትራ ወደ ድርጅቱ እንድትመለስ ቀዳሚ እርምጃውን መውሰድ ያለባት ኢትዮጵያ መሆን ይኖርባታል። እንዲህ ዓይነቱ እርምጃ መውሰድ ደግሞ የኢትዮጵያን ታላቅነት የሚያሳይ እንጂ የኢትዮጵያን ክብርና ሞገስ የሚቀንስ አይሆንም። ይህ በበይነ መንግስታቱ ደረጃ የሚወሰድ እርምጃ የኤርትራ መንግስትን ባህርይ ሊለውጥ የሚችል ብሎም ደረጃ በደረጃ በተባበሩት መንግስታት ዘንድ የተጣለበትን ማእቀብ ለማንሳት ስለሚረዳው ጠቃሚነቱና ለወደፊቱ ሊከፈት የሚችለውን የጋራ ግንኙነት ወይም በሦስተኛ ወገኖች እገዛ ሊመጣ የሚችልን የዲፕሎማቲክ ግንኙነትን እያጠናከረ ሊሄድ ይችላል። ተነሳሽነቱ ግን አሁንም በኢትዮጵያ መንግስት ዘንድ መወሰድ ይኖርበታል።

6. ኢትዮጵያ አሁንም ሌላ ተጨማሪ አዎንታዊ የዲፕሎማቲክ ጀስቸር እርምጃዎችን ለመውሰድ ዝግጁ መሆንዋንና ይህም የሚወሰነው የኤርትራ መንግስት በሚወስደው አጸፋዊ እርምጃና በሚያሳየው አዎንታዊ ግብረ መልስ እየተመዘነ እንደሚሆን በይፋ መግለጽ መቻል ይኖርበታል። ለምሳሌ ኢትዮጵያ <<የኤርትራ መንግስትን ለማጥቃት ፍላጎት ወይም እቅድ እንደሌላት፣ ይልቁንም አዎንታዊ ግንኙነቱ እየተሻሻለ የሚሄድ ከሆነ ኢትዮጵያ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የኤርትራ ወደቦችን ለመጠቀም እንደምትፈልግ፣ የሕዝብ ለሕዝብና የመንግስት ለመንግስት ግንኙነቱን ለማሻሻል እንደምትፈልግ፣ ኢትዮጵያ ለኤርትራ መንግስትም ቢሆን የኤሌክትሪክ ኃይልን ለመሸጥ እንደምትፈልግ ወዘተ…>> የመሳሰሉ እቅዶችን በይፋ መግለጽ ትችላለች። እንዲህ ዓይነቱ መግለጫ የኤርትራ መንግስት ካንዴም ሁለቴ ሊያስብበትና አዎንታዊ መልስ ሊሰጥበት ይችላል።

7. በኤርትራ መንግስት በኩል ደግሞ በተግባር ላይ ሊውል የማይችለውን <<የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ አሁኑኑ ይተግበርልኝ>> የሚለውን ጥያቄ ለጊዜው ቢተወውና ከላይ በጠቀስኩዋቸው ጉዳዮች ላይ በማተኮር

ግንኙነቱን ለማሻሻል ቢንቀሳቀስ ይጠቅማል። የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ እንደሆነ ብዙ አወዛጋቢ ጉዳዮችን የሚያስነሳና የሁለቱን ሕዝቦች ዘላቂ ጥቅምና ትስስርን ከግምት ውስጥ ያላስገባ የግብር ይውጣ ስራ ውጤት ስለሆነ <<አሁኑኑ ወደ ተግባር ካልተለወጠ!>> የሚለው የኤርትራ መንግስት አቋም በቀጣዩ ጊዜ ሊታይ ይችላል። አሁን ግን የድንበር ኮሚሽኑ ጉዳይ ላጠቃላይ ግንኙነቱ ደንቃራ ሆኖ እንዲቀጥል የኤርትራ መንግስት መፍቀድ የለበትም።

የሁለቱም አገራት ፍጥጫና ቅራኔ ለቀጣዩ ትውልድ መተላለፍ የለበትም። ለሁለቱ አገራትና ሕዝቦች ግንኙነት መበላሸት ላለፈው 130 ዓመታት ሲደራረብና ሲባባስ በመምጣቱ ምክንያት መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባትና ያሁኑ ትውልድም የችግሩ አንድ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰድ በመሆኑ መፍትሔውን ማምጣት ያለበት ይህ ትውልድ ነው። ያሁኑ ትውልድ እንደችግር አስቀጣይ አካል ሆኖ በተሳተፈበት ጉዳይ ላይ ቀጣዩ ትውልድ ወራሽ የመሆን ግዴታ የለበትም።